# አጭር የዐውደጥናት ዘገባ

የትምህርት ጥናትና ምርምር ተቋም በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ በሚገኙ የተወሰኑ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች ካሰራጨው መጠይቅ ያገኘውን ጥቆማ መነሻ በማድረግ Workshop on Testing with Particular Reference to Testing in Addis Ababa High Schools በሚል ርዕስ ላይ ግንቦት 29 እና 30/84 ዓ.ም. ዐውደጥናት አካሂዷል።


በዚህ ዐውደጥናት ከሶስት የአዲስ አበባ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች የተውጣጡ 25 ርዕሰ መምህራን፣ ምክትል ርዕሰ መምህራንና መምህራን የተካፈሉ ሲሆን ከእነዚህም መሀከል አምስቱ ከአዲስ ከተማ ሁለተኛ ደረጃ፣ አስሩ ከዳግማዊ ምኒልክ ሁለተኛ ደረጃ፣ የተቀሩት አስሩ ደግሞ ከየካቲት 12 ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች የመጡ ነበሩ። የዐውደጥናቱ መሪዎቹም ከአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ዶ/ር አየለ መሸሻ፣ አቶ ዳንኤል ደስታና አቶ ደሳለኝ ጫልቺሳ ነበሩ። ዐውደጥናቱም የተከፈተው በዶ/ር በኩረ ፀ/ሰማያት የዩኒቨርሲቲው አካዳሚክ መርሐግብር (ፕሮግራም) ኦፊሰር ሲሆን በዚሁ የመክፈቻ ስነስርዓት ወቅት ዶ/ር ዳርጌ ወሌ፣ የትምህርት ጥናትና ምርምር ተቋም ዳይሬክተር፣ አቶ ኃይሌ ሸወር፣ የአዲስ አበባ አስተዳደር አካባቢ የትምህርት መምሪያ ኃላፊ፣ አቶ ብንሣ ባይሣ፣ የአስተዳደር አካባቢው የትምህርት መምሪያ ምክትል ሥራ አስኪያጅ፣ እንዲሁም አቶ ተፈራ ቢተማ፣ የአስተዳደር አካባቢው የትምህርት መምሪያ የኢንስፔክሽን አስተባባሪ ተገኝተዋል።



የዐውደጥናቱ መክፈቻ ሥነሥርዓት በከፊል


ዐውደጥናቱ በአምስት ንዑስ አርዕስት የተከፈለ ነበር ። እነሱም የሚከተሉት ናቸው ።

- Meaning, Purposes and Nature of Student Evaluation: An Overview
- Stating Objectives and Planning a Classroom Test
- Constructing Objective Type Questions
- Administering Tests, Scoring Test papers
- Describing Student Test performance



የዐውደጥናቱ ተሳታፊዎች በከፊል

ከፍ ብለው በተጠቀሱት ንዑስ አርዕስት ላይ የተዘጋጀ ፅሁፍ ለተሳታፊዎቹ ታድሏል፤ በእያንዳንዱም ንዑስ ርዕስ ላይ ባለሙያዎች ማብራሪያ ሰጥተዋል፤ ከልምዱ የተገኙ ምሳሌዎችንም ለአብነት አቀርበዋል ።



የዐውደጥናቱ ተሳታፊዎች በክፍል

ትምህርቱ ቲዎሪ ላይ የተመሠረተ ቢሆንም በተግባር ያጋጠሙ ችግሮችን አካትቶ እንዲቀርብ ተደርጓል:: ከዚህ በተጨማሪ እስከተቻለ ድረስ ለምምዱ እንዲጨመርበት ጥረት ተደርጓል:: በመጨረሻም የትምህርቱ አቅራቢዎችና ተሳታፊዎች ውይይት ካካሄዱ በኋላ የዐውደጥናቱ ተሳታፊዎችም ዐውደጥናቱን በተመለከተ የተዘጋጀ መጠይቅ ሞልተዋል::

ዐውደጥናቱ ሲጠናቀቅ በቦታው ተገኝተው የመዝጊያ ንግግር ያደረጉት አቶ ኃይሌ ሽመር ሲሆኑ በዚህ ስነስርዓት ወቅት በዶ/ር ጓርጊ ፀሌ እና በአቶ ኃይሌ ሽመር አማካይነት የምስክር ወረቀቶች ተሰጥተዋል::



የዐውደጥናቱ መዝጊያ ሥነሥርዓት በከፊል

ተሳታፊዎቹ በሞሏቸው መጠይቆች ላይ ከሰጧቸው አስተያየቶች የሚከተሉት ይገኛሉ ::

ሀ/ ስለማስተማሪያ ፅሑፍ ብቃትና ጽሑፉ ከሥራቸው ጋር ስላለው ዝምድና

ቀደም ሲል በተጠቀሱት ንዑስ አርዕስት ላይ የተዘጋጀውን ጽሁፍ በተመለከቱት ከተሳታፊዎቹ መሀከል 81 % "ብቁ" ነው ሲሉ የተቀሩት 19 % ደግሞ "መጠነኛ" ነው በማለት አስተያየታቸውን ሰጥተዋል :: ከዚሁ ጋር በማያያዝ ጽሑፉ ከዕለት ተዕለት ሥራቸው ጋር ያለውን ዝምድና 69 % "በጣም የተዛመደ"፣ 25 % "ደግሞ በመጠኑ የተዛመደ" መሆኑን ገልፀዋል ::

ለ/ ስለትምህርቱ አቀራረብ ሂደት፣ ሁኔታና የመለመጃዎች ብቃት

የትምህርቱን አቀራረብ ሂደት አስመልክቶ ከተሳታፊዎቹ መሀከል 51 % "መካከለኛ" በሆነ ፍጥነት መከናወኑን፣ 47 % ደግሞ "ጥድፊያ" የነበረበት መሆኑን ገልጸዋል ::

የአቀራረቡንም ሁኔታ በተመለከተ 62% "ከቀላል ወደ ከባድ" ማምራቱን፣ 23% "ከባድ ነገር ያየለበት" መሆኑን፣ የቀሩት 15% ደግሞ "ከባድ ከቀላል ጋር በሚገባ ያልተሳካበት" እንደነበር ጠቁሟል።

ስለመልመጃዎቹም /Exercises / የብቃት ደረጃ ከተሳታፊዎቹ መሀከል 43% "በቂ"፣ 27% "መጠነኛ"፣ 16% "አነስተኛ" ናቸው ሲሉ የተቀሩት /4%/ ደግሞ ምንም አስተያየት ሳይሰጡ ቀርተዋል።

ሐ/ <u>ለዐውደጥናቱ ስለተሰጠው ጊዜ</u>

አብዛኞቹ /64%/ ተሳታፊዎቹ ለዐውደጥናቱ የተሰጠው ጊዜ "አነስተኛ" መሆኑን ጠቁመዋል። የቀሩት /32%/ "መጠነኛ" ነው ሲሉ፣ 4% ደግሞ "በቂ" በማለት አስተያየታቸውን ሰጥተዋል።

መ/ ተሳታፊዎቹ ያላቸውን ማንኛውንም አስተያየት እንዲሰጡ ለቀረበላቸው open-ended ጥያቄ ከጻፏቸው መልሶች ውስጥ ጥቂቶቹ የሚከተሉት ናቸው።


- "በዐውደጥናቱ ላይ የተጠቀሱ፣ የቀረቡ ነገሮች እጅግ በጣም ጠቃሚ ናቸው ብዬ ባምንም የተሰጠው ጊዜ አናሳ በመሆኑ እንደልብ ተወያይቶ ለመማማር አለተመቸምና ጊዜው ሰፋ ቢል የተሻለ ይመስለኛል"
- "የዚህ ዓይነቱ Workshop ለሁሉም ት/ቤቶች የሚዳረስበት መንገድ ቢፈለግ ጥሩ ነው"
- "የዐውደጥናቱ ጊዜ ከማጠሩና በዚህም የተነሳ ገለጻ ባልሆኑት አንዳንድ ርዕሶችና ንዑስ ርዕሶች ለመወያየት ካለመቻሉ በስተቀር ለትምህርቱ ሥራ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደርጋልና ቀጥሉበት እላለሁ"።

<u>ማጠቃለያ</u>

ከተሳታፊዎቹ አስተያየት አንፃር ሲታይ ዐውደጥናቱ ጠቃሚ ነበር ለማለት ይቻላል። ሆኖም፣

- የዚህ የዐውደጥናት ጊዜ / duration / ቢራዘም
- አቀራረቡም ደረጃ በደረጃ /ከቀላል ወደ ከባድ/ እንዲሆን የበለጠ ጥረት ቢደረግ እንዲሁም
- መልመጃዎቹ የበለጠ ቢዳብሩ

የዐውደጥናቱ ጥቅም ከፍተኛ እንደሚሆን ይገመታል።



የወደፊቱ አቅጣጫ ሲጤን